ትምህርት 12

## ስለ ጸሎት (ክፍል 1)

### ፀሎት ምንድነው/ምንን ያሳያል?

ስለ ጸሎት ምንነት እዚህ ላይ ሁሉም ባይዘረዘርም አንዳንድ ዋና ዋና ነገሮች ከዚህ በታች ሰፍረዋል፡፡

1. ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመኑ ምክንያት ወደ እግዚአብሔር ፀጋ ዙፋን ፊት በእምነት በመቅረብ ከእግዚአበሔር ጋር የተቀደሰ ግንኙነት በማድረግ ለመነጋገር በእግዚአብሔር የተሰጠ መልካም ዕድልና ይህንኑ ዕድል የመጠቀም ሂደት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች የአኗኗር ዘይቤ ነው፣ ዮሐ 1፡12፣ ሮሜ 8፡15፣
   ንግግሩ ኃጢአትን መናዘዝና ንስሃ መግባት፣ ለእግዚአብሔር የተገባውን ምስጋናና ውዳሴ ማቅረብ፤ የእግዚአብሐርን ፈቃድ/ምሪትን እንዲሁም ልዩ ልዩ ስጦታዎችንና እርዳታን መጠየቅ፣ ለራስና ለሌሎች ሰዎች የሚስፈልግ ነገር የሚጠየቅበት ወይም የምልጃ ጸሎት የሚደረግበት፣ ክፉ መናፍስትንም በመቃወም ከበረከትና ሕይወት ዙሪያ ለማራቅ የሚጠረግበት ነው፡፡
2. እግዚአብሔር እንዲገዛን፣ እንዲመራን፣ እንዲጠቀምብን፣ ጉዳያችን/አገልግሎታችን እንደፈቃዱ እንዲሆን ፈቃደኝነታችንን የምንገልጽበት ነው፡፡ 2ቆሮ 10፡3-5

3. በእርሱ ችሎታ ታላቅነትና በለጋስነቱና በቃሉ እውነተኛነት ያለን እምነት/መተማመን ጥንካሬ የሚታይበት...... በእርሱ የምንተማመን፣ በጸሎት የጠየቅነውን እንደ ሚሰማን/እንደ ሚሰጠን የምናምን ከሆነ እጃችን እስከ ሚገባ ድረስ መጸለይ አናቋርጥም፡፡
4. ከእርሱ የሆነው በነ ስጦታና ፍጹም በረከት ለኛ ሊሰጠን ፈቃዱ ቢሆንም በጸሎት ካልጠየቅን ስለ ማንቀበል ለመቀበል ከኛ ከሚጠብቁ ጉዳዮች አንዱ መጸለይ ነው፡፡

5. ለእርሱና ለሰዎች ያለን ፍቅር ደረጃ አንዱ መገለጫ ነው፡፡ ሁለት የሚዋደዱ ሰዎች ብዙ ጊዜ አብረው ሆነው ይታያሉ/አይለያዩም/ሲራራቁም ለመገናኘት ይነፋፈቃሉ፣ ይነጋገራሉ፣ አንዱ የሌላው ድምጽ መስማት ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔርን ስንወድና የውለታው ብዛት ሲገባን ወደ ፊቱ በመቅረብ ማመስገን፣ ማወደስ፣ ማክበር፣ ማምለክ የየእለት ተግባራችን ይሆናል፡፡ መጀመሪያ መግባት/መጠመድ ያለብን ወደ አገልግሎትና የግል ጉዳዮቻችን ላይ አይደለም፡፡ ራሳችንንም ጨምሮ ከሁሉም በላይ መውደድ ያለብን እግዚአብሔርን ነው፡፡ ጸሎት የዋለልን ውለታ በማነሳሳት ከልብ በፍቅር ምስጋናችንን የምንሰዋበት ነው፡፡ ታላቅ ሰራውና ማንነቱን በማነሳሳት በእርሱ ታላቅነት በመደነቅ፣ በመርካትና በመመካት የምናወድስበት ነው፡፡

6. ለእግዚአብሔር ክብር ያለን ቅናት፣ ለወገኖቻችን ሕይወትና በረከት ያለን መቆርቆር የምናሳይበት ነው፡፡ ወደ ጌታ ላልመጡትና በተለያየ ችግር ላሉት ማንኛውም ክርስቲያን ማድረግ የሚችለው ቀላሉ ነገር ስለ እነርሱ መጸለይ ነውና፤
   ለአምላካችን ክብር የምንቆረቆር ከሆነ ብዙዎች ቢድኑና በቤቱ ቢጸኑ አምላካችን ስለ ሚከብር በዚህ ጉዳይ እንጸልያለን፡፡ 1ነገ 3፡5-14፣ 2ሳ11፡10-11፣ 10፡9-12
7. እግዚአብሔርን እንደ መለኮታዊ ወዳጅ/አባት እንዳወቅነው የሚገለጥበት/ነገራችንን ሁሉ የምናዋየው ታማኝ ምስጢረኛችን እና ዋስትናችን እንዳደረግነው ማሳያም ነው፤
8. ያገኘነው እርሱን የመጠየቅ ያልተገባን ዕድል/ፕሪቪሌጅ/ በመጠቀም የተሰጠንን የተስፋ ቃል እንዲፈጽም የምንጠይቅበት ነው፡፡ ሉቃ 11፡5-13
9. ስለ ራሳችንና ቤተሰባችን እንዲሁም ስለ ሌሎች ወገኖቻችን ጉዳይ ድርሻችንን ማለትም ከእኛ የሚጠበቅብንን ተወጥተን ቀሪውን የእርሱን ድርሻ በፊቱ አኑረን ከስጋትና ከመጨናነቅ የምናርፍበት መንገድ ነው፡፡ፊሊጵ 4፡6-7

**ከጸሎት ጋር የተያያዙ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮች**

- በሰዎች ላይ ክፉ እንዲሆን በመፈለግ መጸለይ፣ (መራገም)፤
    - ለሚያሳድዱ በመጸለይ ፈንታ፣ ማቴ 5፡44-45
    - የሚረግሙንን በመባረክ ፈንታ፣ ሉቃ 6፡28፣ ሮሜ 12፡14
    - ክፉ ለሚያደርጉብን መልካም በማድረግ ፈንታ፣ ሮሜ 12፡17፣ 21፣ 1ጴጥ 3፡9
- በክፉ ዓለማዊ ምኞት ላይ ያተኮረ ጸሎት፡ - ምድራዊ የግል ብቻ የሆነ ጥቅም/ክብር፣ ድሎት፣ ሃብት ለማከማቸት፣ ገናናነት ለመቀዳጀት የስልጣን ጥማት ለማርካት; ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት የሚደረግ፤ የጽድቅን ሕይወት መሻት ቅድሚያ ያላደረገ ጸሎት፣ ያዕ 4፡3፤
- አለመጸለይ ወይም ጸሎቱ ቶሎ ሳይመለስ ሲዘገይ እየጸለዩ በመቀጠል አለመጽናት፤ ያዕ 4፡1-4

- መነሻ ሃሳቡ በሰዎች ዘንድ ለመታየትና ከበሬታ ማግኘትን መሰረት ያደረገ ለሰዎች መታየት ሚያስችል፤ ቦታ በመምረጥ በየመንገዱ ማዕዘን ቆሞ መጸለይ ሳይሆን ማግኘት የማይቻልበት ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ለሰዎች በማይታይ ስፍራ ሆኖ መጸለይ፡፡ ማቴ 6፡5-6
- ራስን በማጽደቅ ወይም ከሌሎች ሰዎች የተሻሉ አድርጎ በመቁጠር መጸለይ፤ ሉቃ 18፡9-14፣
- ኃጢአትን በመደጋገም መጽናት ሕይወት ላይ ሆኖ መጸለይ፤ ኢሳ 58፡2-5፤
- በእምነት በመጽናት ፈንታ ጥርጣሬ ማስተናገድ፡፡ ማቴ 21፡21-22፣ ያዕ 1፡6-8፤
- እንደ ፈቃዱ ያልሆነ ጸሎት ማቅረብ፤ 1ዮሐ 5፡14 ማንኛውም የእግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆነ ነገር መጠየቅ ላይ ያተኮረ ጸሎት፤

- በእግዚአብሔር ፊት የተወሰኑ መልካም ተግባራት ፈጽሜያለሁ፣ በተለያየ አገልግሎትም አገልግያለሁና ይሄና ያን በረከት ልትሰጠኝ ይገባኛል ብሎ እግዚአብሔርን መጠየቅ ተገቢ አይደለም፡፡ ለዚህ አይነቱ ጸሎት እርሱ የሚሰጠው መልስ ያላወራረድከው ሂሳብ ስላለብህ ያንን አወራርድ በማለት እግዚአብሔር ለአንድ ሰው እንደ ተናገረው አውቃለሁ፡፡ ማንም ሰው እግዚአብሔር አንዳች ነገር እንዲያደርግለት ግዴታ የሚያስገባ ምንም ዓይነት ፍጹም ጽድቅ ሊኖረው አይችልም፡፡ እግዚአብሔር አንድን ሰው ከዘለዓለም ሞት የሚያድንበት ዋጋ ብቻ በገንዘብ ቢተመን የዚህ ዓለም ሃብት ንብረት ሁሉ ዋጋ በላይ እንደሆነ በቃሉ ገልጾታል፡፡

  ይሄ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ያደረገው ምድራዊና መንፈሳዊ ባርኮት ዋጋ ሰው በምድራዊ ዘመኑ ሁሉ ከፍሎት ሊጨርሰው የሚችል አይደለም፡፡ ማር 8፡36፣ ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚያደርገው መልካም ነገር ከጸጋው የተነሳ ነው እንጂ ሊያደርግልን የተገባን ሆኖ ስላገኘን (ለእኛ የተገባን ሳይከፍልን የቀረ ደሞዝ ስላለን፣ እርሱ ዕዳ ስላለበት) አለመሆኑን ማወቅ አለብን፡፡ ይህ ማለት ግን በፊቱ ፈቃዱን ለማድረግና ለመታዘዝ የሚደክሙትና የማይታዘዙትን በእኩል ይሸልማል ማለት አይደለም፡፡

- **የትህትና ጉድለት፡-**

እግዚአብሔርን በሚያከብሩ ቃላት በትህትና ጸሎትን በማቅረብ ፈንታ ሙግት ዓይነት/ትህትና የጎደለው ጸሎት… (አቀራረባችን ህጻናት በወላጆቻቸው ላይ የሚቀብጡት ዓይነት መሆን የለበትም፡፡) 1ጴጥ 5፡5፣

እስራኤላዊያን ወደ ተስፋዪቱ ምድር በጉዞ ላይ ሳሉ ባጉረመረሙባቸው ጊዜያት ምንም ችግር ሳይደርባቸው አልነበረም። ከነዚያ ካጉረመረሙባቸው ጊዜያት አንዱ ለሶስት ቀናት ውሃ ሳያገኙ በምድረ በዳ ስለተጓዙና ማራም በደረሱ ጊዜ ውሃው መራራ ስለነበር ሊጠጡት ስላልቻሉ ነበር። ዘጸ 15፡22-24

ሌላው ደግሞ ዘኑ 13፡3- 14፡10 ላይ የሚወርሷትን ምድር እንዲሰልሉ የተላኩ ሰዎች ዞረው በዓይናቸው ያዩትን በምድሪቱ ሰፍረው ያሉ ሰዎች ብዙነትና ግዙፍነት፣ ያላቸው የታጠቁት መሳሪያ ከባድነትና ከተሞቹ የተመሸጉ መሆናቸው ከራሳቸው ብዛትና የጦርነት ዝግጅት አናሳነት አንጻር ሲያዩት በርግጥ የሚያስፈራ ሆኖ

ስለ አገኙት ነበር። እነዚህ ሁኔታዎች በሰው ሚዛን አንጻር ሲታዩ ማጉረምረማቸው ሲያንስ ነው የሚሰኝ ነበር። ነገር ግን ከግብጽ ምድር ነጻ ያወጣቸው እግዚአብሔር አይናቸው እያየ ጆሮዋቸው እየሰማ በእርሱ መተማመን እንዲማሩ ሲል ካደረጋቸው እጅግ ብዙ ታምራዊ ስራዎች አንጻር ሲታይ በእግዚአብሔር ባለመተማመን ማስቆጣቸው ጥፋተኞች ያደርጋቸዋል።

ሙሴ በእግዚአብሔር ፊት ለ80 ተከታታይ ቀናት ያውም በምድረ በዳ ምንም ምግብና ውሃ ባለመውሰድ ቢጾምም፣ ምንም ያልተጎዳ መሆኑ ለብዙ ቀናት ውሃና ምግብ ባያገኙም እግዚአብሔር ያለውሃና ምግብም በሕይወት ያኖረናል፤ ብዙ በከባዱ የታጠቁ፣ ግዙፍ ቁመና ያላቸው በሚወርሷት ምድር የተቀመጡ ሰዎችም በእግዚአብሔር ኃይል ታግዘን እናሸንፋለን ብለው ማመን ላይ መድረስ ያለባቸው ጊዜ ነበር።

እግዚአብሔርን የማማረር፣ የመውቀስ፣ የመሚገትና በእርሱም የማጉረምረም መነሻ ምክንያቱ የእምነት ደካማነት/ጽኑ አለመሆን ነው። እምነቱ ጽኑ የሆነ ሰው እግዚአብሔር የሚያስፈልገኝ ወይም በጸሎት የጠየቅሁት ነገር እስካሁን ባያደርግልኝም ማድረጉ አይቀርም ብሎ በመጠበቅ በእምነቱ ይጸናል። ደግሞም እነዚህ ነገሮች የሚያመለክቱት፣ ሰው እግዚአብሔር መልካም ሲያደርግልኝ ይገባኝ የነበረ ሲሆን ከለከለኝ/አዘገየብኝ የሚል ያልተገባ አስተሳሰብ ሲኖረው ነው። እርሱ ማንንም ስለ ማይበድል የለመኑትን ነገር የሚሰጠው የጸጋው ታላቅነት ለማሳየት ነው እንጂ የማንም ዕዳ ስላለበት አይደለም። በተለይም የእግዚአብሔር ቃል አታድርጉ የሚላቸውን እንደ ማጉረምረም ያሉ ነገሮች ማድረግ ተጨማሪ ሌላ ጉዳት በራስ ላይ የሚያስከትል ስለሆነ ከላይ ከተጠቀሱት ነገሮች መቆጠብ ያስፈልጋል።

*ምሳሌ 3፡11-12፣ ልጄ ሆይ፤ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አትናቅ፤ በዘለፋውም አትመረር፤ [12] አባት ደስ የሚሰኝበትን ልጁን እንደሚቀጣ ሁሉ፣ እግዚአብሔርም የሚወደውን ይገሥጻልና።*

*1ኛ ቆሮ 10፡9-10፣ ከእነርሱ አንዳንዶቹ ጌታን እንደ ተፈታተኑና በእባብ ተነድፈው እንደ ጠፉ፣ እኛም ጌታን አንፈታተን። [10] ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳጉረመረሙና በአጥፊው እንደ ጠፉ፣ አታጉረምርሙ።*

እነዚህን በመቀላቀል መጸለይ ወይም ቃል በማውጣት መናገር እምነትን ይበልጥ ከማድከም ውጪ ሌላ ፋይዳ የለውም። ማለትም እነዚህን ነገሮች የሚያዘወትር ሰው እግዚአብሔርን ይበልጥ እያሳዘነ አጋንንትን ደስ እያሰኘ ይሄዳል እንጂ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ በጭራሽ አያስገኙለትም። ሰው የእግዚአብሔርን ክብር በመጋፋት የሚፈልገውን ነገር ከእግዚአብሔር ጠይቆ ለመቀበል የሚያስችል መብት የሚሰጥ ምንም መሰረት የለውም።

ከዚህም በላይ እግዚአብሔር ምንም የማይሳሳት በሚያደርገው ነገር ሁሉ ፍጹም ትክክል ስለሆነ እርሱን በመሚገትም ሆነ በመውቀስ መርታት አይቻልም።

መዝ 92፥15፣ "እግዚአብሔር ትክክለኛ ነው፤ እርሱ ዐለቴ ነው፤ በእርሱ ዘንድ እንከን የለም" ይላሉ።"

ማቴ 5፥48፣ "ስለዚህ የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ።"

1 ዮሐ 1፥5፣ "ከእርሱ የሰማነው ለእናንተም የምንነግራችሁ መልእክት፣ እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም፤ የሚል ነው።"

**እኔ ትህትናን በሁለት ከፍዬ ነው የማየው፦**

**የሰው ትህትና ከሰው ጋር በሚኖር ግንኙነት**

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው በዚህ ምድር በመወለድ እንዲኖር ሲያደርገው አዲስ የተወለደው ሕጻን ምንም የሚያስመካ ጉልበት፤ ዕውቀት፣ ሥልጣን፣ ሃብት ንብረት ...ወዘተ ሳይኖረው ባዶ እጁን እየመጣ ነው። ነገር ግን ሰው እያደገ ሲሄድ ከአንዱ ሰው ሌላው ሰው በተለያየ ምክንያት የሚበላለጥ የስጦታ/የችሎታ/የኑሮ መጠን

ይኖረዋል። ስለዚህ ብዙ በረከት የተሰጠው ሰው፣ ዝቅተኛ ስጦታ እንዳለው ሰው በንግግርና የፊት ገጽታ በማሳመር ብቻ ሳይሆን በተግባር በሚገለጥ ሁኔታ ራሱን ዝቅ በማድረግ እንደ አገልጋይ ሲሆን፣ በሰው ፊት ትሁት ሆነ ማለት ነው። ትህትናው በተግባር ሲፈተን የማይታይ ከሆነ ግን መቅለስለስ (ቅልስልስነተት) ነው እንጂ እውነተኛ ትህትና አይደለም።

### የሰው ትህትና ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖር ግንኙነት

የሰው በእግዚአብሔር ፊት ትሁት መሆንን ስንመለከት፣ ከላይ እንደ ተጠቀሰው ከነበረበት ደረጃ ዝቅ በማለት ሳይሆን ራሱ የነበረበት ትክክለኛ ደረጃ በመያዝ ነው። የሁሉም ሰው ትክለኛ መነሻ ደረጃ ደግሞ አፈር ነው። እግዚአብሔር ሰውን ከአፈር ባያበጃጀውና የሕይወት እስትንፋስ ባይሰጠው እኮ አፈር ብቻ ነበር። ሰው ከላይ ካልተሰጠው በስተቀር ምንም ሊኖረው ስለማይችል ከእግዚአብሔር ያልተቀበለው ከራሱ የሆነ ምንም ነገር እንደሌለ በማወቅ፣ ያለ ጸጋ ስጦታው ባዶነቱን በማየት፣ ያለው ነገር ሁሉና በመንፈሳዊም ረገድ የደረሰበት ደረጃ ሁሉ ከእርሱ ጸጋ የተነሳ የተቀበለው እንደ ሆነ በማሰብ፣ ከአፈር በታች የትም ዝቅ ሊል ስለማይችል፣ እንደ አብርሃም "እኔ አፈርና አመድ ሆኜ ሳለሁ በጸጋህ ብዛት እፊትህ ለመቅረብ/ልጅህ ለመባል ያስቻልከኝ ጌታዬ ሆይ" ሲለውና የዚያኑ ያህል ሲገዛለት ነው በእግዚአብሔር ፊት ትሁት የሚሆነው።

እግዚአብሔር እጅግ ያከበረው አብርሐም እንኳ "እኔ ከንቱ ትቢያና አመድ ሆኜ ሳለሁ" ማለቱን ተቀበለው እንጂ፣ ተው እንደዚያ አትበል ትቢያና አመድ አይደለህም አላለውም። እግዚአብሔር ለሰው በክርስቶስ ኢየሱስ በጸጋው የልጅነት መብት ሰጠው ማለት እግዚአብሔርን እንዳያከብር አደረገው ማለት አይደለም።

በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና ሕዝብ እግዚአብሔር ፊት ለጸሎት ሲቀርቡ ያሳዩት የነበረ ትህትና ሁኔታ ይለያያል። አንዳንዶቹ አማርረውታል፣ አጉረምርመዋል፣ ተሟግተውታል፣ ወቅሰውታል...ወዘተ። በገጠሙዋቸው ጊዜያዊ ችግሮች ምክንያት ስለ አጉረመረሙበት ዘላቂ ርስታቸውን መውረስ አልቻሉም። አንዳንዶቹ ደግሞ እኔ ከንቱ፣ ትቢያና አመድ ሆኜ ሳለሁ (ዘፍ18:27፣) እኛ ሸክላዎች፣ አንተም ሸክላ ሠሪ ነህ፤ ሁላችንም የእጅህ ሥራ ነን፤" በማለት ያልሆኑትን ያህል ራሳቸውን ከፍ ከፍ በማድረግ ፈንታ ተገቢ መነሻ ስፍራቸው የት እንደነበረ በማሳየት አክብረውታል።

ስለዚህ እኛ ያውም ለብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብና አገልጋዮች ያልተደረገላቸውን አንድያ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን የሰዋልን ስለሆነ መውሰድ ያለብን መልካም የሆነውን እግዚአብሔርን የሚያከብረውን ምሳሌ ነው እንጂ የእግዚዚብሔርን ክብር የሚጋፋውን ማጉረምረምና የመሳሰሉትን ማስተናገድ በፍጹም አይገባንም።

የእግዚአብሔር ቃል የሰውን ማንነት ያመሳሰለባቸው ወይም መነሻ ስፍራውን ለማሳየት ከገለጠባቸው ነገሮች ለመጥቀስ ያህል፡ -

*ዘፍ 3:19፣ "አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ፣"*

*ኢሳ 41:14፣ "አንተ ትል ያዕቆብ፣ ታናሽ እስራኤል ሆይ"፣*

*ሆሴ 13:3፣ "ስለዚህ እንደ ማለዳ ጉም፣ ፈጥኖ እንደሚጠፋ የጧት ጤዛ፣ ከዐውድማ እንደሚጠረግ ዕብቅ፣ በመስኮትም እንደሚወጣ ጢስ ይሆናሉ።"*

*ኢሳ 45:8፣9፣ "...እኔ እግዚአብሔር ፈጥሬዋለሁ። [9] "ከዐፈር ሸክላዎች መካከል፣ ከሠሪው ጋር ክርክር ለሚገጥም ወዮለት፤ ጭቃ፣ ሸክላ ሠሪውን፣ 'ምን እየሠራህ ነው?' ይለዋልን? የምትሠራውስ ሥራ፣ 'እጅ የለህም' ይልሃልን?*

*ኢሳ 64:8፣ "ይህም ሆኖ፣ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ አባታችን ነህ፤ እኛ ሸክላዎች፣ አንተም ሸክላ ሠሪ ነህ፤ ሁላችንም የእጅህ ሥራ ነን፤"*

*መዝ 144፥4፣ “ሰው እንደ እስትንፋስ ነው፤ ዘመኑም ፈጥኖ እንደሚያልፍ ጥላ ነው።”*

*ኤር 18፥6፣ “የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ሸክላ ሠሪው እንደሚሠራው፣ እኔ በእናንተ ላይ መሥራት አይቻለኝምን?” ይላል እግዚአብሔር፤ “የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ጭቃው በሸክላ ሠሪው እጅ እንዳለ፣ እናንተም እንዲሁ በእጄ ውስጥ ናችሁ።”*

*ሐሥ 9፡15-16፣ ጌታም እንዲህ አለው፤ “ሂድ፤ ይህ ሰው በአሕዛብና በነገሥታት ፊት እንዲሁም በእስራኤል ሕዝብ ፊት ስሜን እንዲሸከም የተመረጠ ዕቃዬ ነው፤ [16] እኔም ስለ ስሜ ምን ያህል መከራ መቀበል እንዳለበት አሳየዋለሁ።”*

*ያዕ 4፡14፣ “ነገ የሚሆነውን እንኳ አታውቁም። ሕይወታችሁ ምንድን ናት? ለጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ።”*

*ሮሜ 6፥17፣ “ነገር ግን የኀጢአት ባሮች የነበራችሁ ቢሆንም፣ ለተሰጣችሁለት ትምህርት በሙሉ ልብ የታዘዛችሁ በመሆናችሁ፣ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፤”*

*ሮሜ 6፥20፣ “የኀጢአት ባሮች ሳላችሁ ከጽድቅ ነጻ ነበራችሁ።”*

*1 ቆሮ 12፥2፣ “አረማውያን በነበራችሁበት ጊዜ ወዲያና ወዲህ በመነዳት ድዳ ወደ ሆኑ ጣዖታት እንደ ተወሰዳችሁ ታውቃላችሁ።”*

*ገላ 4፥8፣ “እግዚአብሔርን ከማወቃችሁ በፊት፣ በባሕርያቸው አማልክት ላልሆኑት (ለጣዖታት) ባሪያዎች ነበራችሁ፤”*

*ኤፌ 2፥1፣ “እናንተ በበደላችሁና በኀጢአታችሁ ምክንያት ሙታን ነበራችሁ፤”*

*ኤፌ 5፥8፣ “ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ። እንደ ብርሃን ልጆች ኑሩ፤”*

*ቆላ 1፥21፣ “ክክፉ ባሕርያችሁ የተነሣ ቀድሞ ከእግዚአብሔር የተለያችሁ በአሳባችሁም ጠላቶች ነበራችሁ።”*

በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ ታናሽ የሆነውን ሰው ነው እጅግ ታላቅ ከሆነው ጸጋው የተነሳ ከነበረበትና ከወደቀበት ዝቅታ ከፍ ለማድረግ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ መስቀል ሞት ድረስ በተሰራው ስራ ምክንያት የልጅነት መብትና የዘለዓለም ሕይወት ነጻ ስጦታዎች ስለ ሰጠው፣ ከመነሻው በነበረበት ስፍራ ራሱን በማየት ነው በእግዚአብሔር ፊት ትሁት የሚሆነው እንጂ፣ አሁን በጸጋው ከሰጠው የልጅነት ከፍታና የክብር ስፍራ ራሱን በመመዘን መሆን የለበትም። እግዚአብሔርን ልጅህ ነኝና የለመንኩህን ልትሰጠኝ ይገባኛል አይባልም። ሳይገባን ልጆቹ ቢያደርገንም በጸሎት የምንጠይቀው መብትን ሳይሆን ጸጋውን እንዲያበዛልን ነው።

*1 ጴጥ 5፥5፣ “ጕልማሶች ሆይ፤ እናንተም እንዲሁ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርስ በመከባበር ትሕትናን ልበሱ፤ ምክንያቱም፣ “እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።”*

ደግሞም ንስሃ ቢገቡም ኃጢአት ማድረግን ባለመተው፣ እንዲሁም አልጋ ላይ ተኝቶ መጸለይን በእግዚአብሔር ፊት ትህትና የጎደለውና ከልብ ያልሆነ ጸሎት ተደርጎ ይቆጠራል። ሆሴ 7፡14፣

**ጾምን ከጸሎት ጋር አጣምሮ ማከናወን በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን በእግዚአብሔር ፊት ራስን ለማዋረድ (ትሁት ለማድረግ) ጥቅም ላይ ውሏል/ይውላል።** 2ዜና 7፡13-14፣ ማር 9፡29።

*የጾም መንፈሳዊ ጠቀሜታ፡-*

1. ምግብና ውሃ ስንወስድ ምግቡ እስከሚፈጭ ድረስ ከበድበድ ስለሚል መጾም ይህን መጫጫን በማስወገድ መንፈሳችን እንዲነቃቃ ያስችላል፡፡ ከምግብና ውሃ ለተወሰነ ጊዜ መቆጠብ ትኩረትን በጸሎቱ ጉዳይ በማሰባሰብ፣ ከመባከን በመውጣት ከልብ የሆነ ተማጽኖ ለማቅረብ ይረዳል፡፡
2. ምግብ የወሰዱበት ሰዓት እየረዘመ በሄደ መጠን ሰውነት ደከምከም ስለሚል የሚደገፉበት የሰውነት አካል ኃይል ምንኛ ደካማ እንደሆነ ስለሚታይ፣ ያልሆኑትን ያህል ራስን ከፍ ከፍ ከማድረግ በመቆጠብ ሁልጊዜ በማይደክመው እግዚአብሔር በመመካት ለእርሱ ለመገዛት ያመቻቻል፣ እግዚአብሔርም ይህን ራስን እንደ ማዋረድና እንደ ትህትና ያየዋል፡፡
3. በእግዚአብሔር ፊት መጾም ማለት ራስን ለማዋረድና እርሱን ከፍከፍ ለማድረግ ስለሆነ ከምግብ ለተወሰነ ጊዜ በመጾም፣ የራስን ፍላጎት/ፈቃድ በመተው/በመካድ የአምላክን ፈቃድ በማድረግ ለእርሱ ፈቃድ መገዛትን/እጅ መስጠትን የሚያሳይ ስለሆነ፡፡

## እግዚአብሔር ጸሎትን እንዴት ይመልሳል?

1. ያደረገልንን ነገር በድምጽ በመናገር (በሬማ) ያሳውቃል 1ነገ 9፡3፣ 2ነገ 19፡20፣ 20፡25፣ 2ዜና 7፡ 12
2. በተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል (ሎጎስ) ጉዳያችን ጋር የተያያዘውን ቃል ወደ ልባችን በማምጣት፤
3. በተጸለየበት ጉዳይ ተጨባጭ ሆኑ ልዩ ልዩ ታምራዊና ድንቅ ስራዎችን በማድረግ፤ በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በመሙላት፣ ሐሥ 4፡31፣
4. በራዕይና በሕልም የጸለዩበት ጉዳይ እጅ ሲገባ በማሳየት/በመናገር (የተለያዩ ምልክቶች በማሳየት፡
5. ባልታሰበ ምሪት፣ የእስራኤል ሰራዊት ከሳዖል ጋር ጎልያድ ሲያስፈራራቸው በፍርሃት ለውስጣቸው ጩኸት ዳዊትን ላከላቸው፡፡ ዳዊት ጦርነት እንደሚዋጋ እርሱም ሆነ አባቱ አላወቁም/አላሰቡትም ነበር፡፡ ዳዊት ያሰበው ወንድሞቹ ያሉበት ሁኔታ ሊያውቅና ስንቅ ሊያቀብላቸው ነበር፣ እግዚአብሔር ግን ጎልያድን በዳዊት ሊመታው መራው፡፡ 1ሳሙ17፡23-51፤
6. የቀባቸው አገልጋዮችን በመጠቀም በእነርሱ አገልግሎት የሕዝቡን ጉዳይ በማስተካከል፤
7. መላዕክቱን በመላክ (መልዕክት እንዲያመጡልን ወይም በሚያስፈልገን ነገር እንዲያግዙን ለማድረግ፡፡ ለምሳሌ ነብዩ ዳንኤል የጸለየው ጸሎት መልስ የእግዚአብሔር መልአክ ነግሮታል፡፡
8. ሳይታወቀን ጥበቃ በማድረግ/በኛና በጠላት መካከል ጣልቃ እየገባ ጋሻ በመሆን ከጠላት ጥቃት በማዳን/በመከለል፣ እርሱ የሰጠን ሳይመስለን የሚያስፈልገንን በመስጠት፡፡
9. በጸሎት እንዲሰጠን የጠየቅነውን ነገር በቀጥታ እጃችን እንዲገባ በማድረግ እና በሌሎች የተለያዩ መንገዶች የጸሎት መልስ ሊሰጥ ይችላል፡፡

©ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2018 ዓ. ም.